ጥያቄ ወይም እገዛ ይፈልጋሉ? ያነጋግሩን፡-
(202) 787-4044 ወይም
lead@dcwater.com

# የመግቢያ ፈቃድ
# የDC Water የሌድ ውሃ ቱቦ <u>በነጻ</u> መተካት

### ነጻ ምትክ ለማግኘት ሁሉም አስፈላጊ ቦታዎች መሞላት አለባቸው

የሚጠጣ ውሃ ውስጥ ያለ ሌድ ወይም ሌድ የያዙ የውሃ ቱቦዎች ጎጂ ሊሆኑ እና የጤና አደጋዎችን ሊያስከትሉ ይችላሉ። ለዚህም ነው የDC Water በዲስትሪክቱ ውስጥ የሚገኙትን የሌድ የውሃ ቱቦዎችን ለመተካት ሳይታክት እየሠራ ያለው - **በነፃ ለእርስዎ ምንም ወጪ ሳያስከፍል**፣ ነገር ግን የእርስዎ **ፈቃድ** ያስፈልገናል። እነዚህን የሌድ ቱቦዎች መተካት የሕዝብ ጤናን ለመጠበቅ እና ለእርስዎ፣ ለቤተሰብዎ፣ ለነዋሪዎች እና ለማህበረሰቡ የሌድ ተጋላጭነትን አደጋ ለመቀነስ ወሳኝ እርምጃ ነው። ለመቀጠል የእርስዎ ፈቃድ ያስፈልገናል። ይህንን የመግቢያ ፈቃድ ሲፈርሙ DC Water እና ኮንትራክተራችን ወደ ግል ይዞታዎ ገብተው ፍተሻ እንዲያደርጉና የሌድ የውሃ ቧንቧዎችን በአዲስ የመዳብ ቱቦዎች **በነጻ ለእርስዎ ያለምንም ወጪ** እንዲቀይሩ ለመፍቀድ ተስማምተዋል ማለት ነው። በተጨማሪም የDC Water ኮንትራክተሮች ወደ ግል ይዞታዎ ገብተው ቱቦዎ ከሌድ የተሠራ መሆኑን ለማረጋገጥ የውሃ ቱቦዎ የሚገባበት ቦታን ፈትሸው የምርመራ ጉድጓዶች ወይም ቀዳዳዎች ይቆፍራሉ። ይህ ፈቃድ በተጨማሪም በግል ይዞታዎ ላይ ሥራውን እንዳይሰሩ ሊያደርጓቸው ስለሚችሉ ወይም ቧንቧዎችዎን በሚተኩ ሰዎች ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ስለሚችሉ ስለሚያውቋቸው ማናቸውም **የተደበቁ አደጋዎች** ለDC Water ኮንትራክተር ለማሳወቅና ስለ መተኪያ ዕቅዱ ለመወያየት ይስማማሉ ማለት ነው። **እባክዎን ያስተውሉ፡-** በእርስዎ ህንጻ(ዎች) ውስጥ ያሉ ሌሎች የሌድ ቧንቧ ምንጮችን ለመለየት እና እነሱን ለመተካት እንዲያስቡ ከተረጋገጠ የቧንቧ ሰራተኛ ጋር አብረው እንዲሠሩ እንመክራለን።

### የDC Water ኮንትራክተር የሌድ ቱቦውን ለመተካት የሚከተሉትን ያደርጋል (ለይበልጥ መረጃ QR ኮዱን ይመልከቱ)፡-

1. ስለ መተኪያ ዕቅዱ ለማብራራት ከባለቤቱ ወይም ከተወካዩ ጋር መገናኘት፣
2. ለስምንት (8) ሰዓታት አካባቢ የሕንጻዎን የውሃ አገልግሎት መዝጋት፣
3. የዲስትሪክቱ ዋና የውሃ መስመር፣ መቁጠሪያው እና የይዞታው ወሰን አጠገብ መቆፈር እና የሌድ የውሃ ቱቦዎን በመንገድ ላይ ካለው ዋና የውሃ መስመር፣ በሕንጻዎ ግድግዳ ወይም ወለል ውስጥ አልፎ፣ የውሃ ቧንቧው ከሕንጻዎ ጋር ከሚገናኝበት መግቢያ ቦታ ላይ ማላቀቅ፣
4. ቧንቧው ወደ ሕንጻዎ በሚገባበት እና ውስጥ ካለው የውሃ መስመር ጋር በሚገናኝበት ግድግዳ በኩል መንገድ ላይ ካለው ከዲስትሪክቱ ዋና የውሃ መስመር እስከ ህንፃዎ ድረስ አዲስ **የመዳብ የውሃ ቱቦ** መትከል፣
5. የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የቧንቧ መስመር ኮድ አንቀጽ 604.8ን ለማክበር በቆጣሪው ላይ ያለው ግፊት ከ 80 psi በላይ ከሆነ የግፊት መቀነሻ ቫልቭ (PRV) መትከል። ዝቅተኛ ግፊት እንዲዘጋጅ ካልተጠየቀ በስተቀር ግፊቱ በ75 psi ላይ ማዘጋጀት፣ እና
6. ውሃውን ከፍቶ፥ የተቦረቦሩ ቀዳዳዎችን ደፍኖ፣ ቦታውን ወደነበረበት መልሶ እና ከተቻለ የውጪውን ቱቦ ግንኙነት በመጠቀም በውሃ ማጠብ።

### መጠበቅ የሚገባዎት የሚከተሉትን ነው፡-

1. **በመጀመሪያ ኮንትራክተሩ የውሃ ቱቦው የተሠራበትን ቁሳቁስ <u>በነጻ ለእርስዎ ያለምንም ወጪ</u> ያረጋግጣል።** በመጀመሪያ ኮንትራክተሩ ዛፉ ያለበት ቦታ እና የይዞታ ወሰን አጠገብ የሙከራ ጉድጓዶች ይቆፍራል፣ ይህም ግቢዎ ውስጥ ወይም የሕንጻው መስመር ላይ ሊሆን ይችላል። ቱቦው የሚገባበት ቦታ ላይ ፈትሾ የውሃ ቱቦው የተሠራበትን ቁሳቁስ ለማረጋገጥ ወደ ሕንጻዎ ለመግባት ፈቃድ ይጠይቅ ይሆናል። አንድ ጊዜ ከተረጋገጠ በኋላ፣ ከላይ ያሉትን ደረጃዎች ተከትለው የሌድ ውሃ ቧንቧውን ምናልባትም በሌላ ቀን ይቀይራሉ። ከመተከሉ በፊት፣ በጊዜው፣ እና በኋላ ፎቶዎችን እና ቪዲዮዎችን ያነሳሉ።
2. **ኮንትራክተሩ** ድራይዎሎችን፣ ንጣፎችን፣ ግድግዳዎችን፣ አጥሮችን፣ ቁጥቋጦዎችን፣ የእግረኛ መንገዶችን፣ የመኪና መግቢያ መንገዶችን፣ ድንጋዮችን፣ ሳርን፣ አበባዎችን፣ እፅዋትን ወይም ሌሎች በይዞታዎ ላይ ያሉ ቋሚ ነገሮችን **ማስነሳት ሊያስፈልገው ይችላል**። የይዞታ ባለቤቱ/ባለፈቃድ ተወካዩ አትክልቶችንና ሌሎች የግል ቁሳቁሶችን ከሥራ ቦታው ላይ ማንሳት አለበት። በተቻለ መጠን ኮንትራክተሩ ዛፎችን፣ ቁጥቋጦዎችን እና ሌሎች ዕጽዋቶችን ላለመንካት ይሞክራል። የDC Water እና ኮንትራክተሮቹ በይዞታዎ ላይ ያሉ ዕቃዎችን ለማንቀሳቀስ ሊረዱዎት አይችሉም።
3. **ኮንትራክተሩ የግል ይዞታዎን መጀመሪያ እንዳገኘው ወይም ከዛ በተሻለ ሁኔታ ለመተው ይሞክራል። የቤት ውስጥ ሥራ ቦታዎች፡-** ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ፣ ኮንትራክተሩ የቤት ውስጥ የሥራ ቦታዎችን ያጸዳል። ኮንትራክተሩ ቋሚ እድሳቶችን ለማድረግ ቀጠሮ ይይዛል፣ ይህም አስፈላጊ ከሆነ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡- የመግቢያ ፓነሎች መትከል፣ የፕላስተር እና የድራይዎል ጥገና፣ ቀዳዳ መሙላት፣ ከዋና ቀለሙ ጋር በማመሳሰል ፕራይም አድርጎ ቀለም መቀባት፣ እና ነባር ንጣፎችን እና ካቢኔቶችን እንደገና ማልበስ እና መተካት። **ከቤት ውጭ የሥራ ቦታዎች፡-** ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ፣ ኮንትራክተሩ ከቤት ውጭ ያሉትን የሥራ ቦታዎችን ያጸዳል፣ የተቦረቦሩ ቀዳዳዎችን ይደፍናል እና ሥፍራው ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ያደርጋል። ኮንትራክተሩ በተጨማሪም አስፈላጊ ከሆነ የሚከተሉትን የሚያካትት ጊዜያዊ ጥገና ሊያደርግ ይችላል፡- የተበላሸውን ቦታ በተመሳሳይ ቁሳቁስ ወይም በጊዜያዊ አስፋልት መተካት፣ የተበላሹትን የሳር ቦታዎች ለጊዜው በአፈር መሙላት። ኮንትራክተሩ አስፈላጊ ከሆነ የሚከተሉትን የሚያካትት ቋሚ ጥገና ሊያደርግ ይችላል፡- የተበላሹ ጡቦችን፣ ስሚንቶን፣ ግራናይት ድንጋይን ወይም የአስፋልት ዳርቻን፣ የእግር መንገድን፣ የመኪና መግቢያ መንገድን እና ድጋፍ ሰጪ ግድግዳዎችን መተካት። ቋሚ ጥገና ዘር መዝራትን፣ ሳርና አትክልት መተካትን ያካትታል። ቋሚ የእድሳት ሥራው ቀጠሮ ተይዞ በሌላ ጊዜ ይደረጋል። የቋሚ እድሳት ቀጠሮ የሚያዘው ብሎኩ ላይ ያለው ሥራ በሙሉ ሲጠናቀቅ ነው።
4. **በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ DC Water ይህን ሥራ ላይሠራው ይችላል፡-** (1) ሠራተኞች የቧንቧውን ቦታ እንዳይቀይሩ የሚከለክሉ **የተደበቁ አደጋዎች** ካሉ፤ (2) የቦታው ባለቤትነት የሌላ ሰው ከሆነ እና ባለቤቱ ይህን ፈቃድ ለመፈረም **ካልተስማማ**፤ (3) እርስዎ ወይም ፈቃድ ያለው ሰው ኮንትራክተሩ በቀጠሮው ቀን ወደ ቦታው እንዲገባ ካልፈቀዱ፤ ወይም (4) እርስዎ ወይም ፈቃድ ያለው ሰው በቀጠሮው ቀን እና ሰዓት **ቤት ከሌላችሁ** እና ሥራውን ለሌላ ጊዜ ቀጠሮ ሳታስይዙ ከቀራችሁ።
5. **DC Water ለእርስዎ ወይም ቦታው ላይ ላሉ ነዋሪዎች ከተተካ በኋላ የሚጠቀሙት አንድ (1) የውሃ ጆግ እና አንድ (1) ለ6 ወራት የሚቆይ ፊልተር፣ እንዲሁም ሁሉንም የሌድ ቅንጣቶችን ለማስወገድ ቧንቧዎችዎን አፍስሶ ለማውጣት የሚከተሏቸው መመሪያዎች ይሰጥዎታል።**
6. **DC Water የሌድ ውሃ ቱቦዎችን አደጋ በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ያቀርባል።**

**ፍቺዎች፡-**

1. **ሕንጻ**፡- ውሃው የሚደርሰው ሕንጻ፣ እንደ ቤት፣ ቤተ ክርስቲያን፣ የልጅ እድገት ተቋም፣ ወዘተ.
2. **የመዳብ የውሃ ቱቦ፡-** የሚጠጣ ውሃ ለመውሰድ የሚያገለግል የብረት መዳብ ቱቦ።
3. **ኮንትራክተር**፡- አንድ የተወሰነ ሥራ ለመሥራት፣ ለምሳሌ የውሃ ቱቦን ለመተካት የተቀጠረ አንድ ሰው ወይም ኩባንያ።
4. **የዲስትሪክቱ ዋና የውሃ መስመር**፡- ከሕንጻዎች የሚወጡት የውሃ ቱቦዎች ውሃ ለማግኘት ከመንገድ ሥር የሚገናኙበት ውሃ የሚያጓጉዝ ቱቦ።
5. **የተደበቀ አደጋ**፡- በቀላሉ የማይታይ ነገር ግን ጎጂ ሊሆን ወይም ችግር ሊያመጣ የሚችል ነገር። የተደበቁ አደጋዎች ምሳሌዎች ወደ ጓሮ መብራት የሚወስድ የኤሌትሪክ ወይም የጋዝ መስመርን ወይም ለቤት ማሞቂያ ዘይት የተቀበረ የነዳጅ ታንከርን ሊያካትቱ ይችላሉ።
6. **የሌድ የውሃ ቱቦ፡-** ወደ ሕንጻው ውሃ ለማምጣት ከመሬት በታች ከዲስትሪክቱ ዋና የውሃ መስመር ተነስቶ ወደ መጀመሪያው የሕንፃው ማገናኛ ድረስ የሚዘረጋ ከሌድ የተሠራ ወይም ሌድ የያዘ ቱቦ።
7. **የተረጋገጠ ደብዳቤ**፡- በቦታው ባለቤት እና የባለቤቱን ማንነት በሚያረጋግጥ ኖታሪ የተፈረመ ሰነድ።
8. **የግል ይዞታ**፡- ባለቤትነቱ የእርስዎ የሆነ ቦታ።
9. **የቦታ ባለቤት/የተፈቀደለት ሰው**፡- የቦታው ባለቤት የሆነ ሰው ወይም በባለቤቱ ስም እንዲሰራ የተፈቀደለት ሰው።
10. **የሙከራ ጉድጓድ፡-** የግቢውን አካባቢና የግል ዕቃዎችን ሳይነኩ ቱቦ የተሠራበትን ቁሳቁስ ለመመርመር 4 ጫማ በ4 ጫማ ጉድጓድ

**የፈቃድ ቅጹን ይሙሉ፣ ይፈርሙ እና ያስረክቡ፡-**

እባክዎን ይሙሉ (**ፈቃድ** እና **የተደበቁ አደጋዎች**) እና ከታች ይፈርሙ። ይህ ፈቃድ መስጫ ካልተፈረመ በስተቀር DC Water እና ኮንትራክተሩ የሌድ ውሃ ቱቦውን **በነጻ አይቀይሩም**። **ፈቃዱ ከሶስት በላይ ቦታዎችን የሚመለከት ከሆነ የተያያዘውን ይሙሉ**። የሌድ ውሃ ቱቦውን ለመተካት ዝግጁ ስንሆን፣ የDC Water ኮንትራክተሩ ቀጠሮ የመያዣ መመሪያዎቹን ይነግርዎታል። የፈቃድ ቅጹን ለማስረከብ፡-

የርእስ መስመሩ ላይ **"Private Lead Service Line Replacement Project/Name and Address" ("የግል የሌድ አገልግሎት መስመር መተኪያ ፕሮጀክት/ስም እና አድራሻ")** ብለው አንድ ቅጂ ለled@dcwater.com **ኢሜል** ይላኩ ወይም
አንድ የተፈረመ ቅጽ በሚከተለው አድራሻ **በፖስታ** ይላኩ፡-

DC Water - Private LSL Replacement Project
5000 Overlook Avenue, SW, COF Bldg., 5th Floor

**ፈቃድ (አንድ ብቻ ይምረጡ)፡-**

________የመግቢያ ፈቃዱን አንብቤያለሁ እና DC Water እና ኮንትራክተሩ ከታች በተጠቀሰው ይዞታዬ ላይ ያለውን የሌድ የውሃ ቱቦ **በነጻ ለኔ ያለምንም ወጪ** እንዲተኩ ፈቃድ ለመስጠት **እስማማለሁ**። ሥራው በሚከናወንበት ጊዜ እኔ ወይም የተፈቀደለት ሰው እንገኛለን።

________የመግቢያ ፈቃዱን አንብቤያለሁ እና DC Water እና ኮንትራክተሩ በይዞታዬ ላይ እንዲገቡ **አልስማማም**። ለሌድ መጋለጥ በተለይ በነፍሰ ጡር ሴቶች እና በሕጻናት ላይ ከባድ የጤና ችግር እንደሚያስከትል ተረድቻለሁ። ሌድ ኩላሊቶችን እና አንጎልን ሊጎዳ ይችላል እንዲሁም ከነርቭ እድገት ጉድለቶች ጋር ተቆራኝቷል። የኩላሊት ችግርና ከፍተኛ የደም ግፊት ያለባቸው አዋቂዎች ከጤናማ ሰዎች በበለጠ በትንሽ የሌድ መጠን ሊጎዱ እንደሚችሉ ተረድቻለሁ። ስለዚህ፣ ምንም እንኳን በብርቱ ቢበረታታም፣ ከሕዝቡ ጋር በተመሳሳይ ጊዜ የሌድ ውሃ ቱቦ እንዲተካ **አልስማማም**። በመጨረሻ፣ በD.C. ሕግ ቁጥር 22-0241 መሠረት ቤቴ ሲሸጥ ወይም ሲከራይ የሌድ ውሃ ቱቦ እንዳለ ይፋ መደረግ እንዳለበት አውቃለሁ። **የውሃ ቱቦ የተሠራበትን ቁሳቁስ ለማረጋገጥ DC Water አሁንም በይዞታዬ ወሰን አጠገብ በሚገኘው የህዝብ ይዞታ ላይ አንድ ወይም ሁለት የሙከራ ጉድጓዶች መቆፈር ሊያስፈልገው እንደሚችል ተረድቻለሁ፣ ይህም በአትክልት ቦታዬ፣ በመኪና መግቢያ መንገዴ ወይም በመሬቱ አቀማመጥ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል።**

የይዞታ ባለቤት/የተፈቀደለት ሰው ስም፡-________________________ ኢሜል፡- ________________________

ፈቃድ ያለው ሰው (ነዋሪ ወይም ሌላ አካል) ከባለቤቱ ባለ ማረጋገጫ ደብዳቤ ወይም ባለቤቱን እንዲወክሉ የሚፈቅድ እንደ የይዞታ አስተዳደር ስምምነት ዓይነት ሌላ ሕጋዊ ሰነድ **የግድ** ማቅረብ ይኖርበታል። ጥያቄ ካልዎት Lead Free DCን ያነጋግሩ።

ፊርማ፡- ____________________ ቀን፡- ________________ ስልክ ቁጥር፡- __________________

የይዞታው አድራሻ፡- ________________________ መላኪያ አድራሻ፡- ________________________
(የሚመለከት ከሆነ)

☐ **የተጨማሪ ይዞታዎች አድራሻ፡-**

**የተደበቁ አደጋዎች፡-**

ስለ ማንኛቸውም ሥራ የሚከለክሉ ወይም ሠራተኞችን ሊጎዱ ስለሚችሉ የሚታወቁ **የተደበቁ አደጋዎች** (ፍቺውን ከላይ ይመልከቱ) ወይም በቅርብ ጊዜ በግል ይዞታዎ ላይ ስለተደረጉ የቧንቧ ሥራዎች ለDC Water እና/ወይም ለኮንትራክተሩ ማሳወቅዎ ***በጣም አስፈላጊ*** ነው። እባክዎን እዚህ ይዘርዝሯቸው፣ ምንም ከሌለ፣ "ምንም" ብለው ይጻፉ፡-

________________________________________________

________________________________________________



ለጥያቄዎች ወይም ለእርዳታ፣ እባክዎን Lead Free DCን በሚከተለው ያነጋግሩ፡-

(202) 787 - 4044 ወይም lead@dcwater.com

**አባሪ - ለባለ ብዙ ንብረቶች የአድራሻ ዝርዝር**

በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ የበርካታ ንብረቶች ባለቤት ከሆኑ እና በነጻ፣ ምንም ወጪ የሌለበት የሌድ አገልግሎት መስመር መተካት ለሁሉም ንብረቶችዎ በአንድ የመግቢያ ፈቃድ ቅጽ መፍቀድ ከፈለጉ፣ እባክዎ ይህን ቅጽ ይሙሉ እና ከመግቢያ ፈቃድዎ ጋር ያስገቡት።

በቦታው ላይ ያለው ወይም ዋና እውቂያው የመግቢያ ፈቃድ ቅጹ ገጽ ሁለት ላይ ከተጠቀሰው ሰው የተለየ ከሆነ እባክዎ ለእያንዳንዱ ቦታ መገናኛ መረጃ ያቅርቡ።

| የንብረቱ አድራሻ | በቦታው ላይ የሚገኘው ሰው | | | | በቦታው ላይ ያሉ ማናቸውንም የተደበቁ አደጋዎች ይግለጹ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ስም** | **ስልክ ቁጥር** | **አማራጭ ስልክ** | **ኢሜል** | |
| *ምሳሌ*<br>*123 F Street NW* | *Parker Taylor* | *202-111-1111* | *202-222-2222* | *ptaylor@aol.com* | *ከባድ ዝናብ ሲዘንብ ምድር ቤቱ ይጥለቀለቃል* |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |

_________የመግቢያ ፈቃዱን አንብቤያለሁ እና DC Water እና የሥራ ተቋራጩ በቦታዬ ላይ ያለውን የሌድ የውሃ ቱቦ እንዲተኩ ፈቃድ ለመስጠት **እስማማለሁ**። ሥራው በሚከናወንበት ጊዜ እኔ ወይም የተፈቀደለት ሰው እንገኛለን።

የንብረት ባለቤት/የተፈቀደለት ሰው ስም፡-______________________________ ኢሜል፡- ______________________________

ፈቃድ ያለው ሰው (ነዋሪ ወይም ሌላ አካል) ከባለቤቱ ባለ ማረጋገጫ ደብዳቤ ወይም ባለቤቱን እንዲወክሉ የሚፈቅድ ሌላ ሕጋዊ ሰነድ **የግድ** ማቅረብ ይኖርበታል። ጥያቄ ካልዎት LFDCን ያነጋግሩ።

ፊርማ፡- ______________________________ ቀን፡- __________________ ስልክ ቁጥር፡- ________________________